1,000 ብር ዋስትና በማስያዝ ተፈትቷል። አጥናፉ ስለድብደባው እና መቅረጸ ድበጹን (ቴፕ ሬኮርደር) ስለመወረሱ ለፖሊስ ጣቢያው አቤቱታውን አቅርቧል። እጥናፉ ገብረ ኪዳን፣ የአንድ ከፍተኛ ጋዜጣ የቀድሞ ዋና አዘጋጅ የነበረ፣ ታህሣሥ 14/97 ታስሮ በታህሣሥ 22 ቀን ተፈትቷል። ሺፈራው እንሰርሙ በዓመቱ ውስጥ ሦስት ጊዜ ተይዞና ተለቆ ፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ታስሮ ይገኛል።

የጋዜጠኞችን መያዝና መታገት ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት መንግሥት ሐሰተኛ መረጃን፣ የዘር ጥላቻ መቀስቀስን፣ ስም ማጥፋትን ማጉደፍን ፣ እና የሕዝብን መልካም ሥነ ምግባር የሚፃረሩ ጽሑፎችን ስለማተም ያሉትን የሕግ ድንጋጌዎች ይጠቀማል። ነፃ ጋዜጠኞች መንግሥት በእነሱ ላይ ክስ ለመመሥረት ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ የሚመርጣቸውን ክፍሎች ይጠቀማል በማለት ከሰዋል። በዓመቱ ውስጥ ጋዜጠኞች ተከሰዋል፣ ታግተዋል፣ ተቀጥተዋልም።

ለምሳሌ በግንቦት ወር ፣ የሰይፈ ነበልባል ሳምንታዊ አማርኛ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ፣ ልውል ሰቦቃ "በሕገመንግሥታዊ ድንጋጌ ከተቋቋመው ክልል እንዲገነጠል ሕዝብን ለአመጽ የሚያነሰሳ" ነው ብሎ ዐቃቤ ሕግ የቆጠረውን አንድ ግጥም በማተሙ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከስሶ ነበር።

በፈቃዱ ሞረዳ፣ የጦማር ሳምንታዊ አማርዘኛ የግል ጋዜጣ ባለቤት እና ዋና አዘጋጅ የኢትዮጵያን የፕሬስ ነፃነት አዋጅ ጥሰሃል በማለት የፌደራል ዋና ዐቃቤ ሕግ በጥር ወር ከስሶት ነበር ። ክሱ የመነጨው በ1990 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተፈጥሮ ስለነበረው አንድ ረብሻ በ1991 አንድ ጽሑፍ ስለታተመ ነው።

ወሰን ሠገድ ገብረ ኪዳን፣ የኢትኦፕ የአማርኛ ቋንቋ ሳምንታዊ የግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ፣ በ1994 ዓ.ም. ሽብርተኞች በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የትግራይ ሆቴል ላይ ያደረሱትን ጥቃት በማስመልከት ሐሰተኛ ዘገባ አትሟል በመባል በዓመቱ ውስጥ ተከስሶ ነበር።

ቴዎድሮስ ካሳ፣ የኢትኦፕ የአማርኛ ቋንቋ ሳምንታዊ የግል ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረ ፣ ተፈርዶበት የነበረውን የ2ዓመት እሥራት በሰኔ ወር ለመጨረስ ተቃርቦ ሳለ ከ4 ዓመት በፊት በቀረበበት የስም ማጥፋት ወንጀል ክስ የ3ወር ተጨማሪ እሥራት ተፈርዶበት ያንንም ተጨማሪ የእሥራት ጊዜ ከጨረሰ በኋላ ተፈትቷል።

ደባስ ዋቅጅራ እና ሽፈራው እንሰርሙ፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የመንግሥት ንብረት የሆነው የኦሮምኛ ስርጭት ጋዜጠኞች፣ ለኦነግ መረጃ አስተላልፈዋል በማለት በሚያዝያ ወር ተይዘዋል። ሁለቱ ጋዜጠኞች የተያዙት ከሜቱማ ሹማምንት ጋር ነበር (ክፍል 1መን ይመልከቱ)። ከሽፈራው እንሰርሙ በቀር ሁሉም ተፈትተዋል።

በዓመቱ መጨረሻ በፕሬስ ክስ አንድ ጋዜጠኛ በወሕኒ ቤት ነበር፣ 54 እራሳቸው በራሳቸው ላይ በሚኑት ስደት ፣ በአገሪቱ ያሉ ሌሎች በርካታ ጋዜጠኞች የወንጀል ክስ ተደቅኖባቸው ነበር።

ከመንግስት የዜና ማሰራጫ እና ከግል ጋዜጦች በዓመቱ ውስጥ 10 ጋዜጠኞች አገራቸውን ጥለው እንደወጡ ወይም እንደጠፉ ዘገባዎች ነበሩ። ሦስት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች (መሐመድ አህመድ ፣ ኬሪያት እስማኤል፣ እና ለምለም ፈንታ) አገራቸውን ጥለው ወደ ኬንያ ሸሽተዋል የሚሉ ዘገባዎችም ነበሩ። ጋዜጠኞቹ ለምን እንደሸሹ ዝርዝሩን ማግኘት አልተቻለም።

መደበኛ/አፈሻል የዜና ማሰራጫዎች በሙሉ ከመንግሥት ድጎማዎች አግኝተዋል። ሆኖም ግን ፣ መደበኛ የዜና ማሰራጫዎች በሕግ ራሳቸውን የቻሉ/ራስ ገዝ እና ለራሳቸው አስተዳደር ኃላፊነት ያላቸው እና በከፊል ገቢም የሚያስገኙ ነበር። የማስታወቂያ ሚኒስቴር የመንግሥት የኦፊሴል ቃል አቀባይ ሆኖ ፣ በመንግሥት ፣ ፕሬስ እና በሕዝብ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ይመራ ነበር። ሆኖም ፣ ከግሉ ፕሬስ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች መልስ መስጠትን መንግሥት አዘውትሮ አሻፈረኝ ከማለቱም ባሻገር ፣ ከፕሬስ ጋር ያለውን ትብብር መንግሥት ከሚያንቀሳቅሰው የኢትዮጵያ አገልግሎት ድርጅት ኢህአዲግ ከሚቆጣጠረው ዋልታ እና ኢንፎርሜሽን ማእከል፣ የዓ ለም አቀፋዊ የዜና ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ወሰኖ ተገኝቷል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ነፃው ፕሬስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት የሚካሄደውን የኦፊሴል እንቅስቃሴ ለመሸፈን ፈፅሞ እንዳይቀርብ በመከልከል፣ ይሄን የሚሸፍኑት የመንግሥት ዜና ማሰራጫ ተወካዮች ብቻ እንዲሆኑ ያደረገውን ውሳኔ ቀጥሎበታል። ዘጋቢዎች አዘውትረው ራሳቸውን በራሳቸው እንደሚቆጣጠሩ አምነዋል።

የሕትመት /የማሳተም ፈቃድ ለማግኘት ጋዜጦች ዓመታዊ ምዝገባ በሚያደርጉበት ጊዜ 10,000 ብር በባንክ ተቀማጭ ያላቸው ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርቡ

የማስታወቂያ ሚኒስቴር ጠይቋል። ይህ የገንዘብ መጠን አንዳንድ አነስተኛ ሕትመቶችን ከመመዝገብ በሚገባ አግልሏቸዋል። አንድ ጋዜጣ ለማቋቋም አሳታሚዎች የአገሪቱ ቋሚ ነዋሪ መሆን እንዳለባቸውም ተጠይቋል። መንግሥት ሌሎች የንግድ ባለቤቶች ቋሚ ነዋሪ እንዲሆኑ አልጠየቀም። አንዳንድ ነፃ ጋዜጠኞች የነዋሪነት ጥያቄው መንግሥት በማስፈራሪያነት የሚጠቀምበት አንድ ዘዴ ነው በማለት ተናግረዋል። የፕሬስ ሕጉ አሳታሚዎች ሁሉ የኅትመታቸውን አንድ ኮፒ በታተመበት ቀን ለማስታወቂያ ሚኒስቴር በነፃ እንዲሰጡ ይጠይቃል።
አብዛኞቹ ነፃ ጋዜጦችና የመንግሥት ጋዜጦችም የሚታተሙት በመንግሥት ማተሚያ ቤቶች ነበር። ያም ሆኖ ነፃው የዜና ማሰራጫ ጽሑፎችን ማተም ስላለመቻሉ ምንም ዘገባዎች አልነበሩም። ፖሊስ ማናቸውንም ማተሚያ ቤት ካለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመዝጋት ሥልጣን ነበረው፣ ነገር ግን በዓመቱ ውስጥ በዚህ ሥልጣኑ አልሠራበትም።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኅበር (ኢነጋማ) እና አመራሩ ዓመቱን ሙሉ እንደታገዱ ነበሩ። ያንኑ ስም የያዘ አዲስ ማኅበር ተቋቁሞ የፍትሕ ሚኒስቴር ባመቻቸው ስብሰባ በጥር ወር 96 ዓ.ም. አዲስ የሥራ አስፈጻሚዎችም ተመርጠው ነበር። በየካቲት 96 ዓ.ም. የፍትሕ ሚኒስቴር አዲስ ለተመረጡት የኢነፕጋማ ዕውቅና ሰጠ። የቀድሞው ኢነጋማ ተወካዮች መንግሥት በመጀመሪያው ማኅበር እና በመሪዎቹ ላይ የጣለውን እገዳ በመቃወም፣ እገዳው ሕገወጥ እና ፖሊቲካዊ ነው በማለት በፍትሕ ሚኒስቴር ላይ ክስ አቀረቡ። ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያው፣ ኢነጋማ እንደነበረ መሥራት አለበት ብሎ አዝዟል። መንግሥት ግን በዓመቱ መጨረሻ ገና ትዕዛዙን አልፈጸመም።

የመንግሥት እና የግሉን ጋዜጠኞች ያካተተው የኢትዮጵያ ሴቶች የዜና ማሠራጫ ማኅበር በዓመቱ ውስጥ የሥራ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ነበር። ማኅበሩ ሥልጠና እና ትምህርታዊ መድረኮችን ከማዘጋጀቱም በላይ፣ አንድ መጽሔት አትሟል።

ሀ/ መንግሥት በኢንተርኔት መጠቀምን አላጠበበም።

መንግሥት በዓመቱ ውስጥ የአካዴሚክ ነፃነትን አጥብቧል። መንግሥት ፕሮፌሰሮች በትምህርታቸው በማናቸውም መስክ ምርምር ማድረግ ይችላሉ፣ ነገር ግን የፖሊቲካ ስሜቶችን መደገፍ አይችሉም ብሏል። በሁሉም ደረጃ የሚገኙ መምህራን

ከተመደቡበት የትምህርት ፕላኖች ዝንፍ ማለት አይፈቀድላቸውም ነበር። የአአዩ ተማሪዎች በነገድ ላይ የተመሠረቱ ማኅበሮችን ማቋቋም ተከልክለዋል። በዩኒቨርሲቲው ቅፅር ግቢ የፖሊቲካ እንቅስቃሴ አይበረታታም ነበር። የደንብ ልብስ የለበሱ ፖሊሶች ይታዩ እንደነበረ እና ነጭ ለባሽ የፀጥታ መኰንኖች ተማሪዎችን ለመምሰል ሲሞክሩ ነበር የሚሉ ያልተረጋገጡ ዘገባዎች ነበሩ። የተማሪ አስተዳደሮች የተፈቀዱ ቢሆንም፣ ብዙ ተማሪዎች መንግሥት በመሠረቱ ፖሊቲካዊ ናቸው ብሎ ሊተረጉማቸው ከሚችል የዩኒቨርሲቲው ግቢ እንቅስቃሴዎች ከመግባት ታቅበዋል። በ1994 በኢመማ በተደረገ ስታቲስቲካዊ ጥናት መሠረት፣ በመላ አገሪቱ ውስጥ በሚገኙ 280 ሕዝባዊ ዩኒቨርሲቲዎች እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 90 ከመቶ ያህል የሚሆኑት የትምህርት ቤት ዳይሬክተሮች እና ምክትል ዳይሬክተሮች የገገርው ፓርቲ ወይም የተዘማጆቹ አባላት ነበሩ። በዓመቱ ውስጥ ተማሪዎች እና መምህራን ታስረዋል። (ክፍል 1 መን ይመልከቱ)።

ለ/ በሰላም የመሰብሰብ እና ማኅበር የመመሥረት ነፃነት

ሕገ መንግሥቱ የመሰብሰብ ነፃነትን ይፈቅዳል። ሆኖም፣ በግብር መንግሥት ይህንን ነፃነት አጣብቦታል። ብዙ ሰው የሚገኝበትን ስብሰባ የሚያደራጁ 72 ሰዓታት አስቀድመው ለመንግሥት ማሳወቅ እና ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው። ተቃዋሚ የፖሊቲካ ፓርቲዎች ፈቃድ የተከለከሉ ስለመሆኑ በዓመቱ ውስጥ በርካታ ዘገባዎች ነበሩ። የክልል ባለሥልጣኖች ፈቃድ መስጠትን ካለምክንያት በረጅም ጊዜ ያጓትቱ እንደነበረ እና የተሰጡ ፈቃዶችንም በመጨረሻዋ ሰዓት ይሰርዙ እንደነበርም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘግበዋል።

በዓመቱ ውስጥ ደጋፊዎቻቸውን፣ በተለይ ከስብሰባዎች ሲወጡ፣ የገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች የተዘወተረ እና የተደራጀ ሁከት ሲላማ አድረገዋቸው እንደነበረ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘግበዋል (ክፍል 1ሐ፣ 1መ፣ እና 3ን ይመልከቱ)።

ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ለማድረግ የሚያናውኑዋቸውን ሙከራዎች የወረዳ እና የክልል ባለሥልጣኖች ሆነ ብለው ያሰናክላሉ በማለት መኢአድ፣ ደኢሕዲኀ፣ እና አብኮ ወቅሰዋቸዋል። ነፃው ኢመማ ለማድረግ የሞከራቸው ስብሰባዎች ወይም ሰልፎች የመንግሥት ቁጥጥር እንደቀጠለባቸው ነበር።

የኦሮሞ ዋና ከተማ ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ (ቀደም ሲል ናዝሬት) እንዲዛወር መንግሥት ያደረገውን ውሳኔ እንዲያጥፍ በመጠየቅ ለመማለድ ሜቴማ፣ ለመንግሥት ሹማምንት ካስታወቀ በኋላ፣ ከአዲስ አበባ እና አካባቢዋ 10000 ያህል ኦሮሞዎች የተገኙበትን ሰላማዊ ሰልፍ ታኅሣሥ 24 ቀን 1996 ዓ.ም. በመስቀል አደባባይ አደራጀ። አዛውንት፣ ወጣቶች፣ እና ሴቶችን ጨምሮ በፖሊስ መደብደባቸው እና መታሠራቸው ተዘግቧል። መንግሥት ግን ሜቴማ ያንን ትዕይንት ለማድረግ አስፈላጊው ፈቃድ አልነበረውም ብሏል ሁሉም ተሰላፊዎች ቢፈተሹ፣ በፖሊሶቹ ላይ ምንም እርምጃ አልተወሰደም።

በጥር ወር ኦሮሞ ተማሪዎች በአአዩ ያደረጉት ተቃውሞ ብዙ መቶ አሥራቶችን እና ቀጥሎም የ330 ተማሪዎችን መባረር አስከትሏል። ለ2 ቀናት በቆየው እገታ ከእነዚህ ተማሪዎች ውስጥ ብዙዎቹ ለሰዓታት በኩረት ላይ በጉልበታቸው እንዲንበረከኩ ተገድደዋል (ክፍል 1 ሐን ይመልከቱ)።

በመጋቢት ወር በትግራይ ክልል የአብይ አዲ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ መብራት፣ አመች መንገዶች፣ እና የባንኳ ውሀ የሌላቸው መሆኑን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። ይቅርታ ካልጠየቁ የሰልፉን አዘጋጅዎች እንደሚያሰሩዋቸው ሶስት የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር (ሕወሃት) ማዕከላዊ ኮሚቲ አባላት እንዳስፈራሩዋቸው ተዘግቧል። በዘገባዎች መሠረት መንግሥትም የደህንነት ሠራተኞችን በመላክ ቀጣይ ተቃውሞዎች እንዳይደረጉ ተከላክሏል። በማይጨው እና ሳምረ የትግራይ ከተሞች ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፎች ለማድረግ የቀረቡትን ጥያቄዎች መንግሥት ወድቅ አድርጓቸዋል።

የኦሮሚያ ዋና ከተማ ወደ አዳማ መዛወሩን በመቃወም እና የታገቱት የአአዩ ተማሪዎች እንዲፈቱ በመጠየቅ የዓለማያ የግብርና ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በመጋቢት ወር ያደረጉትን ፈቃድ ያልተሰጠበት የተቀውሞ ሰልፍ ፖሊስ በትኖታል። በፕሬስ ዘገባዎች መሠረት፣ የተቃውሞ ሰልፉ ከዩኒቨርሲቲው ቅፅር ግቢ ከመውጣቱ በፊት ፖሊስ አንዳንድ ተሰላፊዎችን ይዞ አስሯል። በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከተቃውሞ ጋር በተያያዘ በኦሮሞ ክልል ተማሪዎች በሰፊው እንደታሰሩ ያመለከቱ አያሌ ዘገባዎች ነበሩ (ክፍል 1ሐ፣ 1መን፣ እና 5ን ይመልከቱ)።

በደቡብ ክልል ዋና ከተማ በአዋሳ በ1994 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ በተደረገበት ጊዜ ፖሊሶች በደርዘኖች በሚቆጠሩ ሰላማዊ ተቃዋሚዎች ላይ የፈጸመውን ግድያ እና ያደረሰውን ጉዳት ለማጣራት መንግሥት ያደረገውን ምርመራ ውጤት እስካሁን ገና አልገለጸም። በአዋሳ ከተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ጋር በተየያዘ የታሠሩትን ግለሰቦች፣ /አንዳንዶቹ ከማንም ጋር እንዳይገናኙ የተደረጉ፣ ሁኔታ/ እና የደቡብ ክልል የትምህርት ቢሮ ሃላፊን ግድያ በሚመለከት ምንም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት አልተቻለም።

በ1995 ወይም በ1994 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፎችን በኃይል በበተኑት የፀጥታ ኃይሎች ላይ ምንም ቀጣይ እርምጃ አልተወሰደም። ቀደም ባሉት ዓመታት ሕገ-ወጥ ስብሰባዎችን በማድረግ ታግተው የነበሩት ሰዎች እንደታገቱ ይገኙ እንደሆነም በዓመቱ መጨረሻ የሚታወቅ ነገር አልነበረም።

ሕገ መንግሥቱ በማኅበር የመደራጀትን ነፃነት እና ባልተገደበ ሰላማዊ የፖሊቲካ ሥራ መሳተፍን መብት ደንግጓል። ሆኖም፣ መንግሥት ይህንን መብት በግብር አጣብቦታል። መያዶችን በሚመለከት፣ መያዶች ገንዘባቸውን በአንድ ቋት ለማስባሰብ የሚያስችል ትክክለኛ ትስስር መመሥረትን ጨምሮ፣ በርካታ የፖሊሲ ጉዳዮች ሳይፈቱ ቀርተዋል። ሆኖም፣ የመያዶችን ምዝገባ ሂደት በተመለከተ ትንሽ የግልጽነት መሻሻል ነበር። የመጀመሪያ ምዝገባን የሚያስተዳድረው የፍትሕ ሚኒስቴር ነው። መንግሥት ለሰብዓዊ መብቶች ሊግ የሥራ ፈቃድ መስጠትን እንደነፈገ ነው። (ክፍል 4ን ይመልከቱ)።

በሕግ እንደተደነገገው፣ መንግሥት የፖሊቲካ ፓቲዎች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ብምቦ) ዘንድ እንዲመዘገቡ ይጠይቃል። በሁለት ተከታታይ ብሔራዊ ምርጫዎች ያልተሳተፉ ፓርቲዎች ከዝርዝሩ ውስጥ ይሠረዛሉ። 69 ያህል የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነበሩ። 13 ብሔራዊ ፓርቲዎች ሲሆኑ፣ የቀሩት በተወሰኑ አካባቢዎች የሚሠሩ ናቸው። በዓመቱ ውስጥ ምዝገባው የተሰረዘበት ማንም የፖሊቲካ ፓርቲ ስለመኖሩ አልተዘገበም።

በዓመቱ ውስጥ መንግሥት ከሜቴማ ጋር ግንኙነት አላቸው ያላቸውን ሰዎች በተደጋጋሚ ይዞ አስሯል። እሥራቱም ፕሬዚደንቱን፣ ምክትል ፕሬዚደንቱን፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቲ አባላትን እና ሠራተኞችን፣ ሁለት ዘበኞችን ያካተተ ነበር።

አንዳንዶቹ እስራቶች ካለመያዣ ትዕዛዝ የተፈጸሙ ሲሆኑ፣ ፍርድ ቤቶች ተጠርጣሪዎች እንዲፈቱ ቢጠይቁም፣ አንዳንድ እገታዎችም እንደቀጠሉ ነበር። (ክፍል 1መን ይመልከቱ)። በመሥሪያ ቤቱ ላይ ሕገ ወጥ ብርበራ ሰለመደረጉ ድርጅቱ ቅሬታውን ገልጿል። በሐምሌ ወር መንግሥት የሜቴማን የሥራ ፈቃድ አግዷል። ይሄም ድርጅቱ ምንም እንዳይሠራ ያደረገ ሲሆን፣ እርምጃውም የተወሰደው መንግሥት ድርጅቱ፣ በአአዩ አንድ ተማሪ የገደለውን የእጅ ቦምብ ጥቃት ጨምሮ፣ በርካታ የሁከት ሥራዎችን አደራጅቷል በሚለው መሠረት ነው።

ሐ/ የሃይማኖት ነፃነት

ሕገ መንግሥቱ ሃይማኖት ነፃ እንዲሆን ደንግጓል። መንግሥትም በአጠቃላይ ይህንን መብት በግብር አክብሮታል። ሆኖም፣ አንዳንድ ጊዜ የአካባቢው ባለሥልጣኖች መብቱን ጥሰዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን (ኢኦቤ) እና እስላምና፣ የሕዝቡን 90 ከመቶ በማቀፍ፣ ዋነኞቹ ሃይማኖቶች ናቸው።

መንግሥት የሃይማኖት ስብስቦች እንዲመዘገቡ ደንግጓል። የሃይማኖት ተቋሞች በፍትሕ ሚኒስቴር ዘንድ ይመዘገባሉ፣ ምዝገባቸውንም በየዓመቱ ማሳደስ አለባቸው፣ ሆኖም፣ ኢኦቤ ገና መመዝገብ ያለበት ከመሆኑም በላይ፣ እስካሁን ሳይመዘገብ በመቆየቱም ምንም ችግር አልደረሰበትም። በተመሳሳይ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (እጉጠምቤ) በ1987 ዓ.ም. ከተመዘገ በኋላ፣ ስለድንጋጌው ያለውን ቅሬታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አሰምቶ ምንጊዜም ዳግመኛ አለመመዝገቡ ተዘግቧል። በእነዚህ ልዩነቶች ላይ ሌሎች የሃይማኖት ስብስቦች ተቃውሞአቸውን ቢያሰሙም፣ ከመንግሥት በኩል ጉዳዮች በእኩልነት የመያዝ ውጤት አላስገኘም።

በሕጉ መሠረት፣ አንድ የልማት ሥራ የሚጀምር የሃይማኖት ድርጅት የልማት ክንፉን እንደ አንድ መያድ ለብቻ ማስመዝገብ አለበት። የሃይማኖት ስብስቦች ለፀሎት ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ መካነ መቃብር የሚሆን መሬት መንግሥት በነፃ ሰጥቷቸው ነበር። ሆኖም፣ የመሬቱ የባለቤትነት መብት የመንግሥት ሆኖ፣ ለፀሎት ቤቶች ወይም ለመካነ መቃብር ከተመደበው በስተቀር የቀረውን ቦታ በማናቸውም ጊዜ መልሶ ሊወሰደው ይችላል።

ለሃይማኖት ተቋማት የመንግሥት መሬት በመመደብ ረገድ አድልኦ እንደተፈጸመባቸው አናሳ የሃይማኖት ስብስቦች ዘግበዋል። በትክክል ያልተገለፀ ሕገ ወጥ ሥራዎችን ያከናውናል ተብሎ አንድ ባሕላዊ ሃይማኖት አምላኪ የሆነ የኦሮሞ የሃይማኖት ስብስብ አምልኮቱን ተከልክሏል። የስብስቡ መሪዎች ከኦነግ እና ከሜጫና ቱለማ ማህበር ጋር የቅርብ ትስስር አላቸው ተብለው ይጠረጠሩ ነበር። ለቤተ ክርስቲያኖች እና መካነ መቃብር መሬት ሲጠይቁ መድልዎ እንደሚደረግባቸው የፕሮቴስታንት ስብስቦች አልፎ አልፎ ዘግበዋል። ወንጌላዊ መሪዎች መጤዎች ሆነው ሰለሚታዩ፣ ከኢኦቤ እና አጉጠምቤ ጋር ሲመዛዘን መሬት በማግኘት በኩል ችግር እንዳለባቸው ዘግበዋል። መሬት በማግኘት በኩል ከመንግሥት ቢሮክራሲ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የበለጠ ችግር እንደሚገጥመው እስልምና ጉባኤ ጠቅላይ ምክር ቤት የዘገበ ሲሆን፣ ሌሎች ግን የመስጊድ ቦታዎችን በተመለከተ እጉጠምቤ ተጠቃሚ መሆኑን ያምናሉ። ብዙ መስጊዶች ከከተማው መንግሥት ስምምነት ውጭ በቦታው ላይ በተቀመጡ ሰፋሪዎች የተሠሩ በመሆኑ፣ የማፍረስ ዓላማ ሆነዋል።

የውጭ አገር የሃይማኖት ሠራተኞች የአንድ ሃይማኖታዊ ድርጅት የልማት ክንፍ ካልሆኑ መንግሥት ቪዛ አይሰጣቸውም።

የሕዝብ ትምህርት ቤት ባለሥልጣኖች በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሴት ተማሪዎችን ሻሽ ማሰር መከልከላቸው በእስልምና አምልኮ ጣልቃ ገብቷል በማለት አንዳንድ ሙስሊም መሪዎች ባለፉት ጊዜያት ቅሬታ ሲያሰሙ ያቆዩ ቢሆንም፣ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን፣ በክልሎች አካባቢ ጭምር የሻሽ ማሰርን ልማድ የትምህርት ሚኒስቴር በወቅቱ እንደተቀበለው መሪዎቹ ዘግበዋል።

በመንግሥቱ (ኃይለማርያም) አገዛዝ ወቅት የተወረሱ አንዳንድ ንብረቶች ገና አልተመለሱም።

ካለፉት ዓመታት በሚለይ ሁኔታ፣ በዓመቱ ውስጥ በሃይማኖቶች መካከል ሁከት የሚያስከትሉ ግጭቶች አልተከሰቱም።